# በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢሕጤኢ

ጥር 2011 ቅጽ 3 ቁጥር 7

በኢሕጤኢ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## ጊኒ ዎርምን ለማጥፋት እየተደረገ ያለው ዘመቻ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተገለጸ



የኢንስቲትዩቱ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥር ማዕከል ከካርተር ማዕከል ጋር በመተባበር ጊኒዎርምን በሃገር አቀፍ ደረጃ በፍጥነት ለማጥፋት ለባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ከጥር 6 እስከ 8/2011ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ በቢን ሆቴል ተሰጠ።

የስልጠናው ዋና ዓላማ ባለሙያዎችን ተገቢውን የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት ጊኒወርምን የማጥፋት ዘመቻው ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ እና እስከታች በማውረድ በሽታውን በአጭር ጊዜ ከሃገሪቱ በማጥፋት አለም ዓቀፍ የእውቅና ሰርተፍኬት ማግኘት እንዲቻል ነው።

አቶ መስፍን ወሰን በአገር አቀፍ ደረጃ ጊኒወርምን የማጥፋት ፕሮግራም አስተባባሪ በስልጠናውን የመክፈቻ ስነ-ስርዓት ወቅት እንደገለጹት ጊኒዎርምን በሃገር አቀፍ ደረጃ የማጥፋት ፕሮግራም ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ የነበረ ሲሆን በተጠቀሰው ዓመት በተደረገ ጥናት 1130 ሰዎች በላይ በጊኒወርም የተያዙ ሲሆን በሽታውን ለማጥፋት በተደረገው ከፍተኛ ጥረት ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰ መጥቶ በ2018 ዓ.ም በጊኒዎርም አንድም ሰው ሳይያዝ ቀርቷል፤ይህም ትልቅ ስኬትና በቀጣይ ለምንሰራቸው ስራዎች ጥንካሬ የሚሰጥ ነው ብለዋል።

አቶ መስፍን አያይዘውም በአሁኑ ሰዓት ኢንስቲትዩታችን በባለቤትነት በመያዝ ከካርተር ማእከልና ከአለም ዓቀፍ የጤና ድርጅት ጋር በመተባበር በርካታ ስራዎች እየተሰሩ የሚ

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪዎች የአቅጣጫ መቆጣጠሪያ ተገጠመላቸው

የኢንስቲትዩቱን የተለያዩ ስራዎችን በተሻለና በፍጥነት ተግባራዊ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪዎች ላይ የአቅጣጫ መቆጣጠሪያ /GPS/ በማስገጠም ወደ ስራ መግባቱ ተገለጸ።

አቶ አብይ ንጉሴ የኢንስቲትዩቱ ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር መቆጣጠሪያውን በኢንስቲትዩቱ ተሽከርካሪዎች ላይ መግጠም ያስፈለገበትን ምክንያት ሲያብራሩ እንደገለጹት ኢንስቲትዩቱ 160 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ያሉት ሲሆን ከብዛታቸው አንጻር ሹፌሮች የት እንዳሉ፣ምን እየሰሩ እንደሆነ፣በታዘዙበት ቦታ ተገኝተዋል አልተገኙም፣ከስራ ሰዓት ውጭ የሚንቀሳቀሰውና ከፍጥነት በላይ የሚያሽከረክረው የትኛው ሹፌር ነው የሚሉትንና የነዳጅ ፍጆታን ለመቆጣጠር ስለተፈለገ በብዛት መስክ ላይ በምንጠቀምባቸው 90 ተሽከርካሪዎች ላይ /GPS/ በመግጠም ወደ ስራ ተገብቷል።

መቆጣጠሪያው በተሽከርካሪዎቹ ላይ የተገጠመው በታህሳስ ወር 2011 ዓ.ም ቢሆንም ወደ ስራ የተገባው ግን በጥር ወር መሆኑንና በከፍተኛ ደረጃ ስራዎች እንዲቀንሱ እና አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎች እንዲገቱ ከማድረጉም በላይ ሹፌሮችም በስራቸው ላይ በሰዓቱ ተገኝተው ለመስራት እንዲችሉ ትጋትን እና ጥንቃቄን እንዲጨምሩ ማድረግ መቻሉን ዳይሬክተሩ አያይዘው የገለጹ ሲሆን በሌላ በኩል የመቆጣጠሪያ ሲስተሙ በነዳጅ ፍጆታ በኩል ተቋማትን በ25 በመቶ ትርፋማ እንደሚያደርግ በሳይንስ የተቀመጠውን በቀጣይ ኢንስቲትዩቱ ምን ያህል ትርፋማ እንደሆነ የሚገመገም መሆኑን ተናግረዋል።

የመቆጣጠሪያ ሲስተሙ ለአሰራር አስቸጋሪ እንደሆነ የተወራ ነገር ቢኖርም ዳይሬክቶሬቱ ግን ይህ አለመሆኑ በማመን ጠንክሮ ወደ ስራው ገብቶ በመተግበር ላይ ይገኛል ብለዋል አቶ አብይ።

# የደንጉ ትኩሳት ወረርሽኝ ሱማሌ ክልል መከሰቱን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

ኢንስቲትዩቱ በሱማሌ ክልል ፊቅ ዞ
ን ለገሂዳ ወረዳ የደንጉ ትኩሳት ወ
ረርሽኝ  መከሰቱን አስታወቀ::

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬ
ክተር ዶክተር በየነ ሞገስ ዛሬ በሰ
ጡት መግለጫ የደንጉ ትኩሳት ወ
ረርሽኝ በክልሉ ከወራት በፊት በዶ
ሎ አዶ ወረዳ ተከስቶ የነበረ ሲሆን
በአሁኑ ወቅት በለገ ሂዳ ወረዳ ተ
ከስቷል::

በወረርሽኙ 60 ሰዎች መጠቃታቸ
ውን ከተያዙት 60 ሰዎች ውስጥ
41ዱ ህፃናት ሲሆኑ 19ኙ ደግሞ
አዋቂዎች ናቸው ብለዋል::

የክልሉ ፈጣን የህክምና ምላሽ ሰ
ጪ ቡድን በወረርሽኙ ለተጠቁ ሰዎ
ች የህክምና አገልግሎት እየሰጠ ሲ
ሆን ወረርሽኙ በምን ምክንያት እን
ደተነሳ ፈጣን የዳሰሳ ጥናት እየተደ
ረገ መሆኑን ተናግረዋል::

እንዲሁም የኢንስቲትዩቱ ፈጣን የ
ህክምና ምላሽ ሰጪ ቡድን ለተጨ
ማሪ እገዛና ወረርሽኙን ለመቆጣጠ
ር ወደ አካባቢው መላኩንም ገልጸ
ዋል::

በወረርሽኙ በተጠቁ ሰዎች ላይ ከፍ
ተኛ የሆነ ራስ ምታት፣ ነስር፣ የሰ
ውነት ላይ ሽፍታ፣ ከዓይን ጀርባ ከ
ፍተኛ ህመም፣ በጡንቻና በመገጣ
ጠሚያዎች ላይ ህመም፣ ማቅለሽለ
ሽና ማስታወክ ምልክት እንደታየባ
ቸውም ገልጸዋል::

ኢንስቲትዩቱ በአካባቢው የተከሰተ
ው ወረርሽኝ የደንጉ ትኩሳት መሆ
ኑን ለማረጋገጥ የደም ናሙና ወስ
ዶ ምርመራ እያደረገ መሆኑን የተ
ናገሩት ዶክተር በየነ፤ ለተጨማሪ
ምርመራ የደም ናሙናው ወደ ሲኔ
ጋል ዳካር ወይም ኡጋንዳ እንደሚላ
ክም ገልጸዋል::

እንደ ዶክተር በየነ ገለጻ በጥቂት ሰ
ዎች ላይ በተለየ ሁኔታ አደገኛ የ
ደንጉ ትኩሳት ምልክቶች የሚታይ
ባቸው ሲሆን ከ3 እስከ 7 ቀን ድረ
ስ ደም የቀላቀለ የማያቋርጥ ትውከ
ት፣ ከፍተኛ የሆድ ህመም፣ ወደላ
ይ መተንፈስና የድድ መድማት አ
ጋጥማቸዋል::

እንዲህ ዓይነት ምልክት የሚታይ
ባቸው ሰዎች ከ24 እስከ 48 ሰዓ
ት ድረስ ህክምና ካላገኙ ለህልፈተ
ህይወት ሊዳረግ እንደሚችልም ገ
ልጸዋል::

በሽታው የሚከሰተው "ኤደስ" በተባ
ለ የወባ ትንኝ አማካይነት ሲሆን በ
ተለይ ቀን ላይ የመናከስ ባህርይ እ
ንዳላቸው የገለጹት ዶክተር በየነ በ
አካባቢው የሚኖሩ ሰዎች ሙሉ ሰ
ውነታቸውን የሚሸፍን ልብስ እንዲ
ለብሱም መክረዋል::

በበሽታው ተይዞ የዳነ ሰው ቫይረሱ
በሰውነቱ ውስጥ ተደብቆ የሚኖር
ሲሆን ቆይቶም ቢሆን ቫይረሱን ወ
ደ ጤነኛ ሰው እንደሚያስተላለፍም
አስረድተዋል::

በተያዘው ዓመት የለገ ሂዳ ወረዳን
ጨምሮ በክልሉ 331 ሰዎች ላይ የ
ደንጉ ትኩሳት ምልክት መታየቱን
ገልጸዋል::

ለደንጉ ተጋላጭ የሆኑና የደንጉ በሽ
ታ ይኖርባቸዋል ተብሎ በሚታሰቡ
አካባቢዎች  አሁን በሽታው የተከሰ
ተባቸውን ጨምሮ የቅኝት ስራዎች
እንደሚሰራም ዶክተር በየነ አክለው
ገልጸዋል::

የደንጉ ትኩሳት ወረርሽኝ ከ2005 እ
ስከ 2009 ዓ.ም ድረስ በድሬደዋ እ
ንዲሁም ከ2007 እስከ 2009 ዓ.ም
ድረስ በሱማሌ ክልል ጎዴና በቀብሪ
ደሃር ዞኖች ተከስቶ እንደነበረም አ
ብራርተዋል::

በዓለም አቀፍ ደረጃ ግማሽ ያህሉ ህ
ዝብ ለደንጉ ትኩሳት ወረርሽኝ ተጋ
ለጭ ሲሆን በዓለም የጤና ድርጅት
ግምት መሰረት በየዓመቱ 390 ሚ
ሊዮን ሰዎች በበሽታው ይያዛሉ ከእ
ነዚህም ወስጥ 96 ሚሊዮን የሚሆ
ኑት ደግሞ ምልክቱ ብቻ የሚታይ
ባቸው እንደሆነ ተገልጿል::

# የኢቦላ በሽታ ወደ ሀገር እንዳይገባ ጥረቶቹ እንደቀጠሉ ናቸው



የኢቦላ በሽታ ወደ ሀገር ውስጥ
እንዳይገባ ለመከላከል ከጤና ሚ
ኒስቴር፣ ከኢንስቲትዩቱ፣ መንግ
ስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ
ተቋማት እና ከባለድርሻ አካላት
የተውጣጡ ባለሙያዎች በኢንስ
ቲትዩቱ በሃገር አቀፍ ደረጃ እየተ
ደረገ ያለውን እንቅስቃሴ አስመ
ልክቶ በየአስራ አምስት ቀኑ መ
ደበኛ ውይይት ይካሄዳል::

በአሁኑ ሰዓት በዲሞክራቲክ ኮን
ጎ በበሽታው የሚያዙ ሰዎች ቁ
ጥር እየጨመረ ከመሆኑም በላይ
አስጊ ደረጃ ላይ ይገኛል:: ነገር ግ
ን ለኢትዮጵያ አስጊ ሁኔታ ላይ
ባይሆንም የተለያዩ የዝግጅት ስ
ራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ:: በውይ
ይቶቹም ላይ በሽታው ወደ ኢት
ዮጵያ እንዳይገባ ለመከላከል ቦሌ
ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊ
ያን፣ በአራት አለም አቀፍ አውሮ
ፕላን ማረፊያዎች እንዲሁም በ
24 ወደ ሀገሪቱ የመግቢያ በሮች
እየተሰራ ያለውን የስክሪኒንግ እ
ና የክትትል ስራ እይተገመገሙ
ቀጣይ አቅጣጫዎች
ይቀመጣሉ::

# የመጀመሪያው የግሎባል ፋሲሊቲ ድጋፍ ወርክሾፕ በኢትዮጵያ ተካሄደ



መቀመጫውን ፓሪስ ያደረገው የግ
ሎባል ፋሲሊቲ ድርጅት የብሄራዊ
የምግብ መረጃ መተንተኛ መድረክ
(National Information Platform
for Nutrition (NIPN)) ፕሮጀክት
ን ለሚያካሂዱ አስር አገራት የተለያ
ዩ የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆ
ን የመጀመሪያውን አውደ ጥናት በ
አዲስ አበባ አካሂዷል::
ከጥር 22 እስከ 24 2011 ዓ.ም በኢ
ሊሊ ሆቴል አውደጥናቱን ሲካሄድ
የብሄራዊ የምግብ መረጃ መተንተኛ
መድረክ ፕሮጀክት (NIPN) የኢትዮ
ጵያ ቡድን አባላት እንዲሁም የተለ
ያዩ አጋር አካላት ተሳትፈዋል::
በወርክሾፑ በዋናነት የብሄራዊ የም
ግብ መረጃ መተንተኛ መድረክ ፕ
ሮጀክትን በሙሉ አቅም ለማስኬድ
የሚያስችል አቅጣጫ ላይ ውይይት
የተደረገ ሲሆን በስነምግብ ፖሊሲ
ጥያቄ አወጣጥና አቀራረብ እንዲሁ
ም የመረጃ ማጠናቀርና ትንተና ሂ
ደትን በተመለከተ የአቅም ግንባታ
ስልጠና ለፕሮጀክት ቡድን አባላትና
ለአጋር አካላት ተሰጥቷል::
በተጨማሪም የብሄራዊ የምግብ መ
ረጃ መተንተኛ መድረክ (NIPN) ፕ
ሮጀክት ቀጣይ ሂደት ላይ ውይይት
ተደርጓል::
የግሎባል ፋሲሊቲ ከሕብረተሰብ ጤ
ና ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር ባ
ዘጋጁት በዚህ አውደጥናት ላይ ከግ
ሎባል ፋሲሊቲ የመጡ የተለያዩ ባ
ለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን ልምድ
ና እውቀታቸውን አካፍለዋል::
የግሎባል ፋሲሊቲ ቡድን መሪ ማ
ርቲ ቫን ሊሬ ፣ የምግብ ዋስትና ባ
ለሙያዋ ፔሪን ጊኒዝ ፣ የኢፒዲሞ
ሎጂ ባለሙያው ጁሊያን ቻሊምባ
ውድ እንዲሁም የግሎባል ፋሲሊ
ቲ አማካሪ ዩሱፍ ኬይታ ውይይቱ
ን መርተዋል::
በአውደጥናቱ ላይ ተግባራዊ የስነም
ግብ ፖሊሲ ጥያቄ አወጣጥና አቀራ
ረብ ፣ የመረጃ አቀራረብ ትንተናና
ቅንብር ፣ የመረጃ ጥራት እና ቁጥ
ጥር እንዲሁም የመረጃ አያያዝ እ
ና አቀማመጥን በተመለከተ የቡድን
ውይይት ተደርጓል::ለሶስት ቀናት በ
ተካሄደው አውደጥናቱ ላይ 22 ተሳ
ታፊዎች ተገኝተዋል::

## . . . ጊኒ ዎርምን የማጥፋት

ከገጽ 1 የዞረ

ገኙ ሲሆን በቀጣይም በሽታወን በአ
ጭር ጊዜ ከሃገሪቱ ለማጥፋት የሕ
ብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ እና ለባ
ለሙያዎች ተደጋጋሚ ስልጠናዎች
ን በመስጠት እስከ ታች ድረስ ተግ
ባራዊ የሚሆኑ ስራዎችን በተገቢው
ለመስራት የአሰልጣኞች ስልጠና እ
የሰጠን እንገኛለን ሲሉ ሰፊ ማብራ
ሪያ ሰጥተዋል::
አቶ ጌታነህ አብርሃ የኢንስቲትዩቱ
የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቁጥጥ
ር ማዕከል እና የጊኒዎርም የማጥፋ
ት ፕሮግራም ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ
ስልጠናውን አስመልክቶ እንደተናገ
ሩት በ2018 ዓ.ም በጊኒዎርም አን
ድም ሰው አለመያዙ ጥሩ ቢሆንም
በጋምቤላ ክልል በእንሰሳት ላይ መ
ታየቱ በሽታው ያለመጥፋቱን
ያመለክታል ብለዋል::
በዓለም አቀፍ ደረጃ ስንመለከት በአ
ንጎላ፣ በቻድ፣ በማሊ፣ በደቡብ ሱ
ዳን እንዲሁም በኢትዮጵያ በሽታው
ባለመጥፋቱ አለም ዓቀፍ ሰርተፍኬ
ት ያላገኙ ሀገሮች ናቸው በመሆኑ
ም አገራችን ጊኒዎርምን በፍጥነት
በማጥፋት ሰርተፊኬቱን ለማግኘት
ስለ ጊኒዎርም በሽታ በሃገር አቀፍ
ደረጃ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ከፍ ማ
ድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ለባለሙያ
ዎች የአስልጣኞች ስልጠና መስጠ
ጥ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆኖ አ
ግኝተነዋል ሲሉ አቶ ጌታነህ ጨም
ረው ገልጸዋል::
ጊኒዎርምን በተመለከተ ባለሙያዎ
ች ጭምጭምታዎችን ለሚመለከታ
ቸው አካላት በምን መልኩ መስጠ
ት እንዳለባቸው እና የቅኝት ስራዎ
ች ላይ በማተኮር ፍጥነት ያለው የ
መረጃ ልውውጥ ተግባራት እንዴት
እንደሚሰሩ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ
ስልጠና ለመሆኑ አቶ መስፍን በማ
ጠቃለያ ሃሳባቸው ገልጸዋል::
በጊኒዎርም የቅኝት ስራ ላይ ተመ
ድበው የሚሰሩ የሁሉም ክልል ባለ
ሙያዎች፣ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያ
ዎች፣ጊኒዎርምን የማጥፋት ፕሮግ
ራም ግብረሃይል አባላት በስልጠና
ው ላይ የተሳተፉ ሲሆን የካርተር
ማዕከልና የአለም ጤና ድርጅት የቴ
ክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ከማድረግ
ባሻገር ስልጠናውን መስጠት እና በ
ማገዝና ተሳትፎ አድርገዋል::